የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሰላሳ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፻፰
አዲስ አበባ መጋቢት ፳፰ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

**33th Year No.108**
**Addis Ababa 6th April, 2025**


**ማውጫ**


**ደንብ ቁጥር ፻፺፰/፪ሺ፲፯**

**በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሰው ኃይል ስምሪት በልዩ ሁኔታ ለማመጣጠን የወጣ የዝውውርና ምደባ ደንብ ቁጥር ፻፸፱/፪ሺ፲፮ን ለማሻሻል የወጣ ደንብ**

**ገፅ............................................... ፬ሺ፵፬**


**CONTENT**


**Regulation Number 198/2025**

**A Regulation to Amend a Special Condition to Balance Transfer and Placement of Human Recourse Deployment of the Government Institutions of Addis Ababa City Administration Regulation No. 179/2024**

**Page........................................................ 4044**


## ደንብ ቁጥር ፻፺፰/፪ሺ፲፯

## በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሰው ኃይል ስምሪት በልዩ ሁኔታ ለማመጣጠን የወጣ የዝውውርና ምደባ ደንብ ቁጥር ፻፸፱/፪ሺ፲፮ን ለማሻሻል የወጣ ደንብ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት መስሪያ ቤቶች ላይ እየታየ ያለውን የአፈጻጸም ክፍተት እና የመልካም አስተዳደር ችግር ለመቅረፍ በከተማ አስተዳደሩ በሶስቱም የአስተዳደር እርከኖች ላይ ተቋማት በአግባቡ ተልዕኳቸውን ለማሳካት የሚያስችል የተመጣጠነ የሰው ኃይል እንዲኖራቸው ለማድረግ የተጀመረውን የማመጣጠን ተግባር ለማከናወን ተጨማሪ ጊዜ የሚያስፈልገው መሆኑ በመታመኑ፤

## Regulation Number 198/2025

## A Regulation to Amend a Special Condition to Balance Transfer and Placement of Human Recourse Deployment of the Government Institutions of Addis Ababa City Administration Regulation No. 179/2024

**WHERAS,** It is found necessary that additional time is needed to complete the balancing of man power that has been initiated to address the performance gap and good governance problems in government offices in Addis Ababa City Administration, so that institutions at all three administrative levels of the city administration have a balanced human resource to properly fulfil their missions;

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈጻሚ አካላት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፹፬/፪ሺ፲፭ አንቀጽ ፺፬ መሰረት ይህን ማሻሻያ ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ ደንብ "በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሰው ኃይል ስምሪት በልዩ ሁኔታ ለማመጣጠን የወጣ የዝውውርና ምደባ ደንብ ቁጥር ፻፸፱/፪ሺ፲፮ን ለማሻሻል የወጣ ደንብ ቁጥር ፻፺፰/፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪.<u>ትርጓሜ</u>**

የቃሉ ወይም የሐረጉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩."**ደንብ**" ማለት በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሰው ኃይል ስምሪት በልዩ ሁኔታ ለማመጣጠን የወጣ የዝውውርና ምደባ ደንብ ቁጥር ፻፸፱/፪ሺ፲፮ ነው፤

፪. በደንቡ የተተረጎሙ ቃላትና ሐረጎች በዚህ ደንብም ተፈጻሚነት አላቸው፡፡

**፫.<u>ማሻሻያ</u>**

በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሰው ኃይል ስምሪት በልዩ ሁኔታ ለማመጣጠን የወጣ የዝውውርና ምደባ ደንብ ቁጥር ፻፸፱/፪ሺ፲፮ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

፩.በደንቡ አንቀጽ ፳፬ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፳፬ ተተክቷል፤

**"፳፬. <u>ደንቡ በሥራ ላይ የሚውልበት ጊዜ</u>**

ይህ የልዩ ዝውውር እና የምደባ አፈፃፀም ደንብ ከመጋቢት ፳፰ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም ጀምሮ ለአንድ ዓመት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡"

The Addis Ababa City Cabinet has issued this amendment regulation in accordance with Article 94 of Proclamation No. 84/2023, which was issued to determine the powers and functions of the executive bodies of the Addis Ababa City Administration.

**1. <u>Short title</u>**

This regulation may be cited as "Regulation No. 198/2025, A Regulation to Amend a Special Condition to Balance Transfer and Placement of Human Resource Deployment of the Government Institutions of Addis Ababa City Administration Regulation No. 179/2024".

**2. <u>Definition</u>**

Unless the context of the word or phrase indicates otherwise, in this regulation:

1. **"Regulation"** means A Special Condition to Balance Transfer and Placement of Human Recourse Deployment of the Government Institutions of Addis Ababa City Administration Regulation No. 179/2024;
2. The words and phrases so interpreted under the regulation shall also apply in this regulation.

**3. <u>Amendment</u>**

A Special Condition to Balance Transfer and Placement of Human Recourse Deployment of the Government Institutions of Addis Ababa City Administration Regulation No. 179/2024, issued to balance the workforce in government offices under special circumstances, is hereby amended as follows:

1. Article 24 of the Regulation is hereby repealed and replaced with the following new Article 24;

**"24. <u>Coming in to Force</u>**

This Special Transfer and Assignment Implementation Regulation shall be effective for a period of six months from 6th of April, 2025."

**፬.ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከመጋቢት ፳፰ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት ፳፰ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም**

**አዳነች አቤቤ ደሳ**
**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

**4. Effective Date of the Regulation**

This regulation shall enter into force as of this 6th day of April, 2025.

**Done at Addis Ababa, this 6th Day of April, 2025**

**Adanech Abiebie Desa**
**Mayor of Addis Ababa City**